# ከቅንጅት ለአንድነትና ለዴሞክራሲ የተሰጠ መግለጫ

## ቅንጅት ፓርላማ መግባትና አለመግባት የጊዜው ወሳኝ የፖለቲካ ጥያቄ ነው ብሎ አያምንም በጉዳዩም ላይ ቅንጅት እንደ ድርጅት የመጨረሻ ውሳኔ ገና አልሰጠም።

በትላንትናው እለት የኢትዮጵያ ቴሌቪዥን «ኢትዮጵያ ረቪው» የሚባለውን ድህረ ገፅ በመጥቀስ የቅንጅት ሊቀመንበር አቶ ኃይሉ ሻወል «ቅንጅት በመጪው ፓርላማ ላለመግባት መወሰኑን» አስመልክቶ ዘገባ አቅርቧል።

የኢትዮጵያ ቴሌቪዢን የጠቀሰው ድህረ ገፅም ወሬውን እንደ ወሬ ከማቅረቡ በስተቀር በቀጥታ አቶ ኃይሉ ያሉትን አልጠቀሰም። በምን አገባብ (context) እንደተባለም የተገለፀ ነገር ስለሌለ ዘገባው ያልታሰበውን እንድምታ ሊሰጥ ስለሚችልና ይህም በህብረተሰባችን ውስጥ ባጠቃላይና በደጋፊዎቻችን በተለይ ሊፈጥር የሚችለውን ብዥታ ከወዲሁ ለማጥራት በጉዳዩ ላይ ቅንጅቱ ያለውን አቋም ማጥራት አስፈላጊ ሆኖ አግኝተነዋል። ለዚህም እንዲያግዝ የቅንጅቱ ምክር ቤት ከሊቀመንበራችን ከአቶ ኃይሉ ሻወል ጋር በስልክ በመገናኘት በእሳቸው በኩል የተነገረውን እርግጠኛውን ነገር ከተባለበት አገባብ (context) ጋር በማገናዘብ ምክር ቤቱ ይህንን መግለጫ የመስጠቱን አስፈላጊነትና እሳቸውም በሚገኙበት አገር የተፈጠረውን ብዥታ ማጥራቱን አስፈላጊነት ተስማምተንበታል።

በአቶ ኃይሉ በኩል የቀረበው መግለጫ በአጠቃላይ እዚህ አዲስ አበባ በነበሩበት ጊዜ በግል ደረጃ በቅንጅቱ ካውንስል አባላቶች ውስጥ የነበረውን ስሜት በመመልከት፣ ቅንጅቱ ከህዝቡ ጋር ባደረጋቸው ውይይቶች በስፋት የተንጸባረቀውን የህዝብ ስሜት ከግምት በማስገባት፣ ኢሕአዴግ በአገራችን ውስጥ የፈጠረውን የፖለቲካ ቀውስ በሰላማዊ መንገድ ለመፍታት ፍፁም ፍላጎት ማጣት ብቻ ሳይሆን እንዲያውም ውጥረቱን ለማባባስ እየወሰደ ያለውን ፍፁም ከመንግስት የማይጠበቅ ኃላፊነት የጎደለው እርምጃውን በማየት ሊሆን የሚችለውን የቅንጅቱን ውሳኔ እሳቸው በመገመት ያቀረቡት የግላቸው አስተያየት

ነበር፤ ይህ አስተያየታቸውና የተመሰረተበት ጭብጥም በመሰረቱ ስህተት ነበር ለማለት አይቻልም::

ሆኖም ዘገባዎቹ ሲቀርቡ የቀረበውን አስተያየት የቅንጅቱ ካውንስል መደበኛ ውሳኔ እንደሆነ ተደርጎ መተርጎሙ ትክክል አይደለም:: ቅንጅቱ እንደ ድርጅት በአሁኑ ጊዜ ያለው ወሳኝ የፖለቲካ ጥያቄ ፓርላማ መግባት ወይም አለመግባት ነው ብሎ አያምንም:: ዋናው ጥያቄ በአገራችን ዴሞክራሲያዊ ስርዓት ይመሰረታል አይመሰረትም የሚለው ነው:: በተለይ ኢሕአዴግ በግንቦቱ ምርጫ በደረሰበት ሽንፈት ምክንያት በምርጫው ምክንያት ተከፍቶ የነበረውን የዴሞክራሲ ጭላንጭል ለመዝጋትና አገሪቱን ወደ ለየለት አምባገነናዊ ስርዓት ለመውሰድ የሚያደርገው መፍጨርጨርና ይህንንም ላለመቀበል ተቃዋሚ ፓርቲዎች ህዝቡን ከጎናቸው በማሰለፍ እያደረጉ ያለው ትግል አገራችንን አስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ በመክተቱና ይህም አገራችንን ክፉ አዝቅት ውስጥ እንዳይከት መከላከሉ ነው የጊዜው ከባድ የፖለቲካ ጥያቄ:: አገራችን እንዲህ አይነት አደጋ ውስጥ እንዳትገባ በተቃዋሚዎች በኩል እየቀረቡ ያሉትን የሰላም አማራጭ ሀሳቦች ገዢው ፓርቲና መንግስት እንዲቀበሉ መገፋፋቱ ነው የጊዜው ወሳኝ የፖለቲካ ጥያቄ::

በመጪው ፓርላማ መግባትና አለመግባት ከዚህ አጠቃላይ ሁኔታ ጋር አብሮ የሚመለስ እንጂ ለብቻው መልስ ስለተሰጠው የአገራችን የፖለቲካ ውጥረት ይረግባል ብሎ መገመት ፍፁም የዋህነት ነው:: ስለሆነም ቅንጅቱ እስካሁን ድረስ ይህንን ጥያቄ በተናጠል በመመልከት የመጨረሻ ውሳኔ አልሰጠም:: ይህንን ውሳኔ ከአጠቃላይ የአገሪቱ የፖለቲካ ችግር ጋር በመመልከት የዴሞክራሲያዊ ሂደቱን ወደፊት የሚወስዱ የተለያዩ እርምጃዎችን ከሌሎች አጋር ተቃዋሚ የፖለቲካ ድርጅቶች ጋር በመሆን ይወስዳል:: ይህን ጥያቄ ለብቻው መመለስ አስፈላጊ ነው ብሎ በሚያምን ጊዜ ሁሌም እንደሚያደርገው በሰፊው መክሮበት ለአገራችንና ለዴሞክራሲያዊ ሂደቱ ይጠቅማል የሚለውን ውሳኔ በጊዜውና በግልፅ ይሰጣል::

**ቅንጅት ለአንድነትና ለዴሞክራሲ**

**መስረከም 11 ቀን 1997 ዓ.ም.**

**አዲስ አበባ**